## <u>ግጥም</u>

### ከቅጣው

## <u>ገና ነው</u>

ቀኑ እንደሆን አልነጋም

አጀንዳው አልተዘጋም

እንደጨለመ ነው ዛሬም

ድቅድቅ እንዳለ ነው ቀኑ

አላበቃም ትግሉ፤አልተጠቃለለም ድርሳኑ

እና ሓውልቱ ነገ ነው

ዛሬ ሐውልት አትበሉ

ድንጋይ በድንጋይ ብትቆልሉ

ሐሰት እንጂ እውነት አትሉ

የጮሌ ነገር የለበጣ

የፖለቲካ ቁማር ገበጣ

ከትዝብት በቀር አያዋጣ!

ትናንት ለሕዝብ የወደቁ

በግፈኞች የተጨፈለቁ

በአረመኔዎች የተጠቁ

አንጸባራቂ ታሪካቸው

ያልተመለሰው ጥያቄያቸው

ዛሬም ይጮሃል ደማቸው

ለሸንገላ የዋለ ኣጽማቸው

ዛሬም ይጣራል ድምጻቸው

እያዋድቀ ነው ዓላማቸው

ለእነዚያ የአጥቢያ ኮከቦች

የኢትዮጵያ አንድነት ልጆች

የሐቅ ፈር ቀዳጆች

የትግል ቅኝት ዕንቁ ፈርጦች።

የዛሬው ሐውልት አይገልጣቸውም

የእነሱ ነገር መቸ አበቃ

ኧረ ገና ነው ገና ነው ገና

ሐቃቸው በሸፍጥ ተመርጎ

ቃላቸው ዱር ተመስጎ

እውነታችው እኮ ይጮሃል

ድምጻቸው አላረፈ

መስዋዕት መሆኑ አላበቃ

እፎይታ አላስታቀፈ

ትንሳኤያቸው አልደመቀ

ከቁም ነገር አልተጻፈ

ከአባት ለልጅ እያለፈ

እየመረረ እየገዘፈ

እየጋመ እየጦፈ

እውነተኛ ገጹ እየተለየ

ዛረም ሐቅ ነው በግልጽ የታየ

እናም የተስፋዬ፣የአምሃ፣ የዘርጋው የእሷም የእሱ

የጸጋዬ፤የማርቆስ ሌላም ሌላም በየዘርፉ

ዳር እስከ ዳር በየአጥናፉ

ለአንድ ሐገር ለአንድ ሕዝብ

ለመብቱ ለክብሩ ተሰውተው ያለፉ

አልተቋጨም ምዕራፉ

አልታጠፈምና ክንፉ

በጮሌ አንደበት አትለፍልፉ

እውነት ምላሽ አላገኘም

ሐውልት እያላችሁ.. አታጥቁ።

መስታወት መጽሔት/ አዲስ አበባ/ ነሐሴ 1985

## <u>ዛሬም እንደ ጥንቱ አለ!</u>

ከ ቅጣው

ትናንትም ለሞት፤ ዛሬም ለሞት

ለጥፋት ብቻ የታደለ

ይህ መከረኛ ፍጥረት

ዛረም እንደጥንቱ አለ!

በከተማው በገጠሩ

በየፈፋው በየዱሩ

ለዓላማው ጽናት ወጥቶ ወርዶ

ከግፈኞች ተፋልሞ፤ ከሀገር አፍራሾች ተፋርዶ

አይከፍሉ መስዋዕትነትን ከፍሎ

ብዙ ታገለ የግፈኞችን በትር ችሎ

ዛረስ መች አረፈ፤ዓላማውስ መች ተሳካ

ምን አግኝቶ በምን ይርካ!

ያጽናው በላብ በዕውቀቱ

የገነባው በደም በአጥንቱ

ሁሉም ይጥፋ ተባለ

ከላይ ትዕዛዝ ተቀበለ

እንደገና ሀሁ...እያለ

ያ መከረኛ ፍ ጥረት ዛሬም እንደጥንቱ አለ።

መስተዋት መጽሄት/መስከረም 1986/አዲስ አበባ/